**<u>በካንቤራ/አውስትራሊያ በሊቢያና በደቡብ አፍሪካ በአሰቃቂ ሁኔታ ለተሰውት ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን የጸሎት ስነሥርዓት ተደረገ</u>**

በካንቤራ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ የኦርቶዶክስ ሀይማኖት ተከታዮች አዘጋጅነት፣ ካንቤራ የሚገኘው የኢትዮጵያ፣ የኤርትራና የግብጽ ኮሚኒቲ አባላት በተገኙበት በSt. Mark Coptic Orthodox ቤተክርስቲያን የጸሎት ስነሥርዓት ተካሂዷል።



ይህ ሁለት ሰዓታት የወሰደ የጸሎት ስነሥርዓት በቅዱሳን መጽሐፍት ንባብና በመዝሙሮች የታጀበ ነበር። በወገኖቻችን ላይ የደረሰው ጭካኔ የተመላበት ግድያ ያሳዘናቸውና በጸሎቱ ላይ የተገኙ ሁሉ በሁኔታው ቅስማቸው ተሰብሮ፣ ልባቸው አዝኖ እንደነበር በወቅቱ ከነበረው ሁኔታ ለመገንዘብ ተችሏል።

በዕለቱ የጸሎቱን ስነሥርዓት የመሩት አቡን ሚካኤል በዚህ አስከፊ ሁኔታ ያዘኑትን ሁሉ መጽናናትን ተመኝተዋል። ሟቾች ሰማዕታት በመሆናቸው ነፍሳቸው መንግስተ-ሰማያት እንደገባ በመናገር ሀዘንተኞቹን አጽናንተዋል።





በዚሁ ስነሥርዓት ላይ ክቡር አምባሳደር አረጋ ኃይሉ ተፈራና የኢትዮጵያ ኤምባሲ ባልደረቦች የተገኙ ሲሆን፤ የኦርቶዶክስ ክርስቲያን አማኞች አስተባባሪ የሆኑት ዶ/ር ጌታቸው አስገዶም ተሰማም በዕለቱ የቤተክርስቲያኗ ቄስና አገልጋዮች ለሰጡት የጸሎት ስነሥርዓት አገልግሎት አመስግነዋል። እንዲሁም በሽብርተኝነት ለተጠቁት ሟች ቤተሰቦች  እንዲሁም ለኢትዮጵያ መንግስትና ሕዝቦች ጥልቅ ሀዘናቸውን በመግለጽ መጽናናትን ተመኝተዋል።







ከዚሁ ጐን ለጐን በኦክላንድ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በደቡብ አፍሪካና በሊቢያ በኢትዮጵያውያን ላይ የተካሄደውን ግድያ በማውገዝ ሰላማዊ ሰልፍ አድርገዋል።




በዚሁ ሰላማዊ ሰልፍም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክን ሰንደቅ ዓላማ በመያዝ “በደቡብ አፍሪካ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን መገደል ይቁም!” ፤ “አይ.ኤስ. በንጹሀን ወንድሞቻችን የፈጸመውን ኢ-ሰብዓዊ ግድያ እናወግዛለን” ብለዋል።